በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ቅድስት ሥላሴ - ክፍል 3

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com

*<u>ቦታ፡-</u>* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ጳጉሜን ፫ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም.**

# <u>እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ</u>

- የወይን ዛፍ ሥርና ግንድ ቢኖረውም ይህን ብቻ ተመልክተን እውነተኛ ዛፍ ነው ለማለት አያስችለንም፡፡ በርግጥም ሊሆን አይችልም፡፡ እውነተኛ ዛፍ ሊያሰኘው የሚችል ነገር ከሌለው ሊሆን የሚችለው ሰው ሠራሽ ዛፍ ነው፡፡
- በምድር በቅሎ የምናገኘው እያንዳንዱ ዛፍ እግዚአብሔር የሰጠው የራሱ የሆነ ሕይወት አለው፡፡ ይህም ሕይወት ከሥሩ ወጥቶ ወደ ግንዱና ወደ ቅርንጫፎቹ ይደርሳል፡፡ ይህም የዛፉ ሕይወት ለዛፉ የተለየ ቅርጽና ልዩ የሆነ ጣእም ያለው ፍሬ እንዲኖረው ያስችለዋል፡፡
- ሕያው የሆነ እግዚአብሔርም የባሕርይ ሕይወቱን ነገር ማወቅ ጎልው ሆኖ የመኖሩን ነገር እንድንረዳ ያስችለናል፡፡
- እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ “ጌታ ግን መንፈስ ነው፤ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ፡፡” <u>*ካል ቆሮ 3፡17፡፡*</u> “ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፡፡” <u>*ዮሐ 4፡23፡፡*</u>
- መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ ሕይወት ነው፡፡ አብ ልብ፣ ወልድ ቃል እንደሆነ ሁሉ የሥላሴ ሕይወት (እስትንፋስ) መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ “ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው፡፡” <u>*ዮሐ 6፡63፡፡*</u> “እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፡፡” <u>*ካል ቆሮ 3፡18፡፡*</u>

# እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

- የወይኑ ዛፍ ሕይወት ከሥሩ እንደ ወጣ ሁሉ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ወጥቷል (ሰርጿል)። "ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል።" ዮሐ 15፡26።
- በእግዚአብሔር ወልድ በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት መኖር ማለት በእግዚአብሔር አብ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መኖር ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን የሚኖርም ከሆነ መልካም የሕይወትን ፍሬ ማፍራት ይቻለናል።
- "በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም። እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል። …" ዮሐ 15፡4-5፡8።
- "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም።" ገላ 5፡22-23።

ማጠቃለያ

- የሥላሴ ሕይወት (እንስትንፋስ) መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪ ነው። "የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ።" ኢዮ 33፡4።
- እኛ የምንኖረው መልካም ፍሬ የምናፈራው፣ መልካም ሥራም የምንሠራው በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ነው።
- በመንፈስ ቅዱስ ማመን ማለት በሰዎች መካከል ታላቅ ሥራን በሚሠራው ኃይል ባለው በእግዚአብሔር መንፈስ ማመን ማለት ነው።
- ሐዋርያትን በዓለም ድንቅ ሥራ እንዲሠሩ ያበቃቸው መንፈስ ቅዱስ ነው። "በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር። … ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤ በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር። ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ።…" የሐዋ ሥራ 2፡1-47።

# በሦስትነት አንድነት

*የሥላሴ አንድነት*

- የወይንን ዛፍ በአግባቡ ለመረዳት እንዲያስችለን፡-
    1. የማናየውን ክፍሉን ሥሩን፡- እርሱም የዛፉ አባት ነው፣ የዛፉ ሕይወት የወጣውም ከርሱ ነው፡፡
    2. ግንዱ፡- የዛፉን ኀልውና የሚያረጋግጥ ከሥሩ የተወለደ ነው፡፡
    3. የዛፍ ሕይወት የወጣው ከሥሩ መሆኑን መረዳታችንን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡
- ስለ ቅድስት ሥላሴም
    1. አብ፡- የቃሉ ወይም የወልድ አባት መንፈስ ቅዱስን ያሰረጸ
    2. ወልድ ፡- ከእግዚአብሔር አብ ቅድመ ዓለም ያለ እናት ድኅረ ዓለም ደግሞ ያለ አባት ከእናት የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ
    3. መንፈስ ቅዱስ፡- ከአብ የወጣ የእግዚአብሔር መንፈስ መሆኑን በጥቂቱ መረዳት ያስፈልጋል፡፡
- እስከሁን እንደተመለከትነው አንዱ የወይን ዛፍ ብቻውን የሆነ የአንድ እግዚአብሔር ምሳሌ አድርገን ተመልክተናል፡፡
- አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አንልም፡፡
- ቅድስት ሥላሴ በስም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ፣ በአካል አብም ወልድም መንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል፣ በግብር አብ መውለድ ማስረጽ፣ ወልድ መወለድ፣ መንፈስ ቅዱስ መስረጽ (መውጣት)፣ በኩነት አብ በልብነት፣ ወልድ በቃልነት መንፈስ ቅዱስ በሕይወትነት (በእስትንፋስነት) ሦስት ስንል አንድ እግዚአብሔር ብለን በማመን ነው፡፡
- የምናመልከው አንድ እግዚአብሔር የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ የሆነ አንድ እግዚአብሔር ነው፡፡ “የአብርሀምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ፥ የአባቶቻችን አምላክ፥ እናንተ አሳልፋችሁ የሰጣችሁትንና ሊፈታው ቈርጦ ሳለ በጲላጦስ ፊት የካዳችሁትን ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው፡፡” ***የሐዋ ሥራ 3፡13፡፡***

# በሦስትነት አንድነት

***የእግዚአብሔር (ሥላሴ) አንድነት በብሉይ ኪዳን***

1. እግዚአብሔር አብርሃምን እርሱን ብቻ እንዲከተልና እንዲያመልከው ለይቶ ጠርቶታል፡፡ "እግዚአብሔርም አብራምን አለው፦ ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ።" ***ዘፍጥ 12፡1፡፡*** አብርሃምም፡-
   - አባቱንና የአባቱን ጣዖት ትቶ እግዚአብሔርን አምልኮታል፡፡
   - እርሱና ዘሩም እግዚአብሔርን አምልከዋል፡፡
   - ዘሩም እግዚአብሔርን ትተው ሌሎች አማልክት ባመለኩ ጊዜ እግዚአብሔር ለጠላቶቻቸው አሳልፎ ሰጥቷቸዋል፣ በምርኮም ወድቀዋል፡፡
2. ለሙሴ ከተሰጡት ትዕዛዛት አንዱ በአንድ እግዚአብሔር ማምለክ ነበር፡፡ "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወድዱኝ፥ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና።" ዘጸአ 20፡3-5፡፡
3. በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር ማመን የሙሴ መጻሕፍት (ኦሪት) እምብርት ትእዛዝ ነበር፡፡ "እስራኤል ሆይ፥ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ። እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፥ በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው። በእጅህም ምልክት አድርገህ እሰረው በዓይኖችህም መካከል እንደክታብ ይሁንልህ። በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው።" ***ዘዳግ 6፡4-9፡፡*** እነዚህ ጥቅሶች "the Shema" ወይም "ስማዕ እስራኤል" ተብለው ይታወቃሉ፡፡ አይሁድ ይህን ቃል በቃል ወስደው የሕግጋቱን ቃል "tephillin" ይሉታል ጽፈው በመጠቅለል በግራ ክንዳቸውና በግንባራቸው ያስሩት ነበር፡፡ ዘዳግ 6፡4-9፣ ዘዳግ 11፡18-21፣ ዘጸአ 13፡8-10፣ ዘጸአ 13፡14-16 ጥቅሶች የሚገኙበትን ጥቅልል ደግሞ "mezzuzzah" የሚሉትን ደግሞ በመቃናቸው (በበራቸው) ላይ ያደርጉት ነበር፡፡ ይህን በማድረግም በአንድ እግዚአብሔር ማምለካቸውን ይመሰክራሉ፡፡ ዛሬ ኦርቶዶክሳውያን በአንገታችን የምናስረው የአንገት ክር(ምልክት) የተወረሰውም ከዚሁ ነው፡፡

# <u>በሦስትነት አንድነት</u>

***<u>የእግዚአብሔር (ሥላሴ) አንድነት በብሉይ ኪዳን</u>***

4. በትንቢተ ኢሳይያስ እግዚአብሔር አንድነቱን “ታውቁና ታምኑብኝ ዘንድ *<u>እኔም</u>*እንደሆንሁ ታስተውሉ ዘንድ፥ እናንተ የመረጥሁትም ባሪያዬ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም ከእኔም በኋላ አይሆንም።” ኢሳ 43፡10። “እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም።” *<u>ኢሳ 44፡6</u>* “ከእኔ ሌላ አምላክ አለን? አምባ የለም ማንንም አላውቅም።” *<u>ኢሳ 44፡8</u>* “እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም ሌላ ማንም የለም ከእኔም በቀር አምላክ የለም በፀሐይ መውጫና በምዕራብ ያሉ ከእኔ በቀር ማንም ሌላ እንደሌለ ያውቁ ዘንድ አስታጠቅሁህ፥ አንተ ግን አላወቅኸኝም እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥ ከእኔም ሌላ ማንም የለም።” *<u>ኢሳ 45፡5-6</u>* “ይናገሩ ይቅረቡም በአንድነትም ይማከሩ ከጥንቱ ይህን ያሳየ ከቀድሞስ የተናገረ ማን ነው? ያሳየሁም የተናገርሁም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ፥ ከእኔም በቀር ማንም የለም። እናንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ፥ እኔ አምላክ ነኝና፥ ከእኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወር በሉ ትድኑማላችሁ።” *<u>ኢሳ 45፡21-22</u>* በማለት ገልጿል።
5. የብሉይ ኪዳን ነቢያት ሁሉ በአንድ አምላክ ያምኑ ,ነበር። ነቢዩ ሚልክያስ “ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን?” *<u>ሚል 2፡10።</u>* ያለ ሲሆን ነቢዩ ዘካርያስም “እግዚአብሔርም በምድር ሁሉ ላይ ይነግሣል በዚያ ቀን እግዚአብሔር አንድ፥ ስሙም አንድ ይሆናል።” *<u>ዘካ 14፡9።</u>* ብሎናል።
6. በራካታዎቹ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች እግዚአብሔርን ቅዱስ አምላክ በማለት ጠርተውታል። “እኔም በበገና ስለ እውነትህ አመሰግንሃለሁ የእስራኤል ቅዱስ አምላክ ሆይ፥ በመሰንቆ እዘምርልሃለሁ።” *<u>መዝ 70፡22</u>*፣ “ተመለሱ፥ እግዚአብሔርንም ፈተኑት፥ የእስራኤልንም ቅዱስ አሳዘኑት።” *<u>መዝ 77፡41</u>*፣ “ኃጢአተኛ ወገንና በደል የተሞላበት ሕዝብ፥ የክፉዎች ዘር፥ ርኵሰትን የምታደርጉ ልጆች ሆይ፥ ወዮላችሁ! እግዚአብሔርን ትተዋል የእስራኤልንም ቅዱስ አቃልለዋል ወደ ኋላቸውም እየሄዱ ተለይተዋል።” *<u>ኢሳ 1፡4</u>*፣ “ሥራውንም ያፋጥን እናውቃትም ዘንድ የእስራኤል ቅዱስ ምክር ትቅረብ፥ ትምጣ ለሚሉ ወዮላቸው!” *<u>ኢሳ 5፡19</u>*፣ “እነሆ፥ የማታውቀውን ሕዝብ ትጠራለህ፥ የእስራኤልም ቅዱስ አክብሮሃልና ስለ አምላክህ ስለ እግዚአብሔር የማያውቁህ ሕዝብ ወደ አንተ ይሮጣሉ።” *<u>ኢሳ 55፡5።</u>*

# በሦስትነት አንድነት

***የእግዚአብሔር (ሥላሴ) አንድነት በሐዲስ ኪዳን***

- ክርስቲያኖች የአብርሃም ልጆች ሆነን በጌታችን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ባለን እምነት የተነሳ በአንድ አምላክ እናምናለን። በጸሎተ ሃይማኖት "ነአምን በአሀዱ አምላክ አሐዜ ኲሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር - ሁሉን በፈጠረ አንድ አምላክ በሆነ … እናምናለን" ብለን የምንመሰክረውም ይኸው ነው። የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትም ይህንኑ እውነት በግልጽ እንደሚከተለው ያስረዱናል።

1. ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ *"ከጻፎችም አንዱ ቀርቦ ሲከራከሩ ሰማና መልካም አድርጎ እንደ መለሰላቸው አስተውሎ። ከሁሉ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ማናቸይቱ ናት? ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥ አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።"* በማለት ያስተማረንን ማር 12፡28-30 እና ማቴ 22፡37 ላይ ተጽፎ እናገኛለን።
2. በወርቃማው ቃሉም *"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ <u>ስም</u> እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"* ማቴ 28፡19። በማለት ስም ብሎ አንድ አምላክ ሥላሴን በመግለጽ ደቀ መዛሙርቱን አዝዞአቸዋል።
3. ስለ አንድ እግዚአብሔር ቅዱስ ጳውሎስም "ወይስ እግዚአብሔር የአይሁድ ብቻ አምላክ ነውን? የአሕዛብስ ደግሞ አምላክ አይደለምን? አዎን፥ የተገረዘን ስለ እምነት ያልተገረዘንም በእምነት የሚያጸድቅ አምላክ አንድ ስለ ሆነ የአሕዛብ ደግሞ አምላክ ነው።" ***<u>ሮሜ 3፡29-30</u>***፣ "ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።" ***<u>ኤፌ 4፡6</u>***፣ "እንግዲህ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ስለ መብላት፥ ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደ ሆነ ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን።"***<u>ቀዳ ቆሮ 8፡4</u>***፣ "መካከለኛውም ለአንድ ብቻ አይደለም እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።" ***<u>ገላ 3፡20።</u>***

# በሦስትነት አንድነት

*የእግዚአብሔር (ሥላሴ) አንድነት በሐዲስ ኪዳን*

4. ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በአንድ አምላክ ስለማመኑና አጋንንትንም አስመልክቶ ስላለውም "እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።" *ያዕ 2፡19* በማለት ጽፎልናል።
5. ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስም "የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው ደሙም ሦስት ናቸውና፤ ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ።" ቀዳ ዮሐ 5፡8።
6. እንደ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትም እግዚአብሔርን ቅዱስ በማለት ጠርተውታል። "ዳሩ ግን። እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ።" *ቀዳ ጴጥ 1፡15*፣ "እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፥ ሁሉንም ታውቃላችሁ።" *ቀዳ ዮሐ 2፡20*፣ "የውኃውም መልአክ። ያለህና የነበርህ ጌታ ሆይ፥ ቅዱስ ሆይ፥ እንዲህ ስለፈረድህ ጻድቅ ነህ፤" *ራእይ 16፡5።*

- በአጠቃላይ በብሉይም ሆነ በሐዲስ በተሰጡን ማስረጃዎች አማካይነት እግዚአብሔር አንድ ነው እንላለን። አንዱ እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችን መውደድ በሥጋችንም በነፍሳችንም ሥልጣን ያለው መሆኑን ማመንም መጻሕፍት ያስተማሩንን ከተረዳነው ሁሉ ይጠበቃል።
- "ቤት ሲሠራ አጥልቆ የቆፈረ በዓለት ላይም የመሠረተ ሰውን ይመስላል፤ ጐርፍም በመጣ ጊዜ ወንዙ ያን ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ ሊያናውጠው አልቻለም።" ሉቃ 6፡48 እንደተባልነው በትምህርተ ሃይማኖት ስለ ሥላሴ ትምህርት በጥቂቱ መሠረት ይዘናል። ይህ ትምህርት ደግሞ ተጀመረ እንጂ አላለቀም አያልቅምም። ቅዱስ ጳውሎስ "ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ።" እንዳለ ቀዳ ቆሮ 13፡12።
- "ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ።" ዮሐ 14፡21 እንዳለን ትእዛዙን በመጠበቅ የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የበለጠ በመረዳት እንዲያጸናን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።

# ጳጉሜን

- ጳጉሜ ማለት ጭማሪ ማለት ነው፡፡ ይህም በዓመቱ መጨረሻ ላይ አምስት ወይም ስድስት ቀን በመሆን የምትመጣ ናት፡፡
- የጳጉሜ ወር ዕለተ ምጽአት የሚታሰብበትም ወር ነው፡፡ ይህም ጳጉሜ የዓመታት መሸጋገሪያ ጨለማው የክረምት ወቅት ወደ ማብቂያው የምናልፍባት እንደሆነች ሁሉ ምጽአትም ከጊዜያዊው ወደ ዘላለማዊ ከምድራዊ ወደ ሰማያዊ ከዚህ ዓለም ወደ ወዲያኛው መሸጋገሪያ ነውና ነው፡፡

- በጳጉሜ ወር የምንጾም ካለን የምንጾመው እንደ ጽጌ ጾም የፈቃድ ጾም መሆኑን መረዳት ይገባል፡፡

- ይህ የጳጉሜን ጾም  ጾመ ዮዲት  በመባል ይታወቃል፡፡

- የዮዲት ጾም የሚባለውም እርሷ ስለ ጾመችው ነው፡፡ ዮዲ 2፡-2-7፡፡

- ዮዲት ባሏ ሞቶባት ከወንድ ርቃ ንጽሕናዋን ጠብቃ በጾም በቀኖና በሐዘን ተወስና ኖራለች፡፡

- በተፈጠረው ጥፋት በሕዝቡ ላይ ለመጣው መከራ ማቅ ለብሳ በራስዋ ላይ ትብያ ነስንሳ ወደ እግዚአብሔር አለቀሰች፡፡ የፍጥረቱን ጥፋት የማይሻ እግዚአብሔር አምላክም ሕዝቡን የሚያድኑበትን መንገድ ለመጠየቅ ሱባኤ በገባች በሦስተኛው ቀን ገለፀላት ***፡፡ ዮዲ 8፡-2 ፡፡***

- ከዚህ በኂላ ጠላታቸውን በዮዲት ምክንያት እስራኤላውያን እስከ ዮርዳኖስ እየተከተሉ አጥፍተዋቸዋል፡፡

- ዮዲት ጠላቷን ለማጥፋት የቻለችው በጾምና በጸሎት ከእግዚአብሔር አምላክ ኃይል አግኝታ ነው፡፡
-
- ስለዚህ ምዕመናን ጥንተ ጠላታችን ሰይጣንን ፈቃደ ሥጋን ለማሸነፍ በጾም ከፈጣሪያችን ኃይልን መጎናጸፍ   አለብን ብለው ጳጉሜን በፈቃድ ይጾማሉ፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org